# መሪያ/ደንብ

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

**ተዛማጅ ምንጮች:** IQA-RA, IQB-RA, IQD, IQD-RB, JEE
**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት:** Office of Teaching, Learning, and Schools

## በትምህርት ቤት አትሌቲክስ ለሚሳተፉ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የትምህርት ብቃት

### I. ዓላማ

በትምህርት ቤት አትሌቲክስ ለሚሳተፉ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሥርዓት-አቀፍ ትምህርታዊ የብቃት መመሪያዎችን ለመለየት

### II. ዳራ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ማህበር እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ መካከል በተደረገው ድርድር መግለጫ መሠረትከመደበኛ ትምህርት ውጭ በማንኛውም የአትሌቲክስ እንቅስቃሴ ለመሳተፍ ለሚመርጡ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ይህ የብቃት መስፈርት ደረጃ የተጠበቀ ይሆናል።በተጨማሪም፣ በሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከአትሌቲክስ ውጪ ሌሎችም እንቅስቃሴዎች ክፍት የምዝገባ ቦታ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፣ በዚህም ትምህርታዊ ብቃት ምንም ይሁን ምን ለሁሉም ተማሪዎች የመሳተፍ እድሎችን ይፈጥራሉ።

### III. ትርጉም

A. የትምህርት ብቃትን የሚጠይቁ የአትሌቲክስ እንቅስቃሴዎች በሞንጎመሪ ካውንቲ ትምህርት ማህበር እና በሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ መካከል ለአትሌቲክስ አበል ብቁ እንደሆኑ የተዘረዘሩ እንቅስቃሴዎች ናቸው።

B. አማካይ 2.0 ማለት በፊተኛው የውጤት መስጫ ወቅት ተማሪው(ዋ) ለተመዘገበ(ች)በት ሁሉም ክፍሎች ዝቅተኛው የክፍል አማካይ ውጤት ነው። የተማሪው(ዋ) አጠቃላይ የክፍል ደረጃ አማካይ ነጥብ (GPA) አይደለም።

C. ወዳቂ ውጤት E እና NC ጨምሮ ተቀባይነት የሌለው የአፈጻጸም ደረጃን የሚያመለክት ማንኛውም ውጤት ነው።

D. የብቁነት ወቅት የሪፖርት ካርድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚቀጥለው የሪፖርት ካርድ እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ የሚቆይ ጊዜ ነው።

### IV. ሂደቶች

A. ብቃት

1. ያፈውን የማርክ መስጫ ወቅት ከአንድ ያልበለጠ የወደቀ(ች)በት ውጤት ጋር የ 2.0 አማካይ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች በሚቀጥለው የማርክ መስጫ ወቅት ለመሳተፍ ወይም ለመለማመድ ትምህርታዊ ብቃት ይኖራቸዋል። በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የመጀመሪያው የማርክ መስጫ

ክፍለጊዜ እንደአማካይ የተወሰደው ውጤት በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሁለተኛ ማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ጀምሮ እንደ ብቃት መመዘኛነት ተግባራዊ ይሆናል።

ብዙ ሰዓት የሚወስድ ኮርስ እንደ አንድ ትምህርትይቆጠራል። የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ውጤት አማካይ ሲያሰላ፣ የብዙ ሰዓት ኮርስ ውጤት ኮርሱ ለተሰጠበት ለእያንዳንዱ ሰዓት አንድ ጊዜ ብቻ የሚቆጠር ሲሆን፤ ለምሳሌ፦ ትምህርቱ የሶስት ክፍለ ጊዜ ኮርስ ከሆነ፣ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ አማካይ ለመወሰን ውጤቱ ሦስት ጊዜ መቆጠር አለበት። ሆኖም፣ ለብዙ ሰዓታት ኮርስ በፊደል የሚገለጸው ውጤት በሪፖርት ካርዱ ላይ አንድ ብቻ ይታያል።

2. በሕጋዊ መቅረት ምክንያት እንዳልተሟሉ ሪፖርት የተደረጉ ውጤቶች እስኪቀየሩ ድረስ እንደ ማለፊያ ውጤት ይቆጠራሉ። የሪፖርት ካርዶች ከተሰጡ በኋላ በ 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ወደ ማለፊያ ውጤት ደረጃ ያልተቀየሩ ያልተሟሉ ውጤቶች እስኪቀየሩ ድረስ ለብቁነት ዓላማዎች እንደ ወዳቂ ይቆጠራሉ።

3. የተማሪ ከኮርሶች መውጣት

   a) አንድ ተማሪ በ 25 ቀናት ውስጥ ወይም ከዚያ ባነሰ ጊዜ ያለ ቅጣት ወይም ሪኮርድ ሳይያዝበ(ባ)ት ከተመዘገበ(ች)በት ኮርስ መተው ወይም መልቀቅ ይችላል/ትችላለች።

   b) አንድ ተማሪ ከ 25 ቀን በኋላ ኮርሱን ሲያቋርጥ/ስታቋርጥ፣ ተማሪው(ዋ) ከኮርሱ በለቀቀ(ች)በት ጊዜ የነበረው/የነበራት ውጤት የሚሰጥ ሲሆን፣ያገኘ(ች)ው ውጤት ለትምህርት ብቁነት ዓላማ ብቻ ወደ ማርክ ክፍለ ጊዜ አማካይ ደረጃ እንዲሰላ ይደረጋል።

4. አንድ ተማሪ ከ MCPS መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ 25 ቀናት የማርክ መስጫ ጊዜ በኋላ ሲወጣ/ስትወጣ፣ተማሪው(ዋ) በሚወጣበት/በምትወጣበት ጊዜ የተገኘው ውጤት ለቀጣይ የስፖርት ወቅት የትምህርት ብቃትን ለመወሰን ተግባራዊ ይደረጋል።

5. አንድ ተማሪ ከ MCPS መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ሲዘዋወር/ስትዛወር እና በኋላ ወደ MCPS ሲመለስ/ስትመለስ፣ ተማሪው(ዋ) ቢያንስ አንድ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ከ MCPS ውጪ ትምህርት ቤት ተምሮ(ራ) ከሆነ፣ ከ MCPS ውጪ ትምህርት ቤት የተገኙ ውጤቶች የትምህርት ብቃትን ለመወሰን ያገለግላሉ። የ MCPS ባልሆነ ትምህርት ቤት ተማሪው(ዋ) ቢያንስ አንድ የማርክ ጊዜ ካላጠናቀቀ(ች)፣ ተማሪው(ዋ) የተማረ(ች)በት ያለፈው የ MCPS ትምህርት ቤት ውጤቶች ብቁነትን ለመወሰን ጥቅም ላይ ይውላል።

6. የሪፖርት ካርዱ በሚሰጥበት ቀን እያንዳንዱ የአትሌቲክስ አስተባባሪ ወይም አሰልጣኝ የተማሪዎችን ብቃት ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች።

7. በመጨረሻው (በአራተኛው) የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ውስጥ በአንድ ትምህርት የወደቀ(ች)በት ውጤት ጋር የ 2.0 አማካይ የሌላቸው የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በፎል ወቅት ብቁ አይሆኑም። ተማሪዎች ያልተሳኩ ኮርሶችን በሠመር ትምህርት ቤት መድገም ይችላሉ። ሆኖም ያልተሳካላቸው ኮርስ በሠመር ክፍለ ጊዜ ካልተሰጠ፣ ተማሪው(ዋ) በዚያው የትምህርት ዓይነት ሌላ ትምህርት ካለ እንዲወስድ/እንድትወስድ ይፈቀድለ(ላ)ታል። ተመሣሣይ ዓይነት ኮርስ ከሌለ ተማሪው(ዋ) እና የተማሪው(ዋ) ካውንስለር በተለዋጭ ኮርስ እና/ወይም የትምህርቱን አይነት ይወስናሉ። የሠመር ክፍለ ጊዜ ውጤት ከበፊተኛው የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ዝቅተኛውን የኮርስ ውጤት ይተካል እና ስለተሳትፎ ዝቅተኛውን 2.0 አማካይ ውጤት ለመወሰን ወደ ስሌት ይገባል።

B. ልዩ ሁኔታዎች

1. ወደ MCPS መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚገቡ ተማሪዎች በሚመዘገቡት የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ ብቁ ናቸው። በአንቀጽ IV.A.1 እንደተቀመጠው ከዚያ በኋላ በእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ ማብቂያ ላይ ብቁነት ይወሰናል።

2. ውጤት በማይሰጥበት ኮርስ አጥጋቢ ያልሆነ ግምገማ ለተማሪ የትምህርት ብቁነት እንደወደቀ(ች) አይቆጠርም።

3. በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአካዳሚክ ብቁ ያልሆኑ ተማሪዎች የብቁነት መስፈርቶችን ለማሟላት ያሻሻሉበትን ማስረጃ ካቀረቡ በሪፖርት ካርድ ላይ የተመዘገበው እንዲለወጥ ከሁለት ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለአሠልጣኙ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰመምህራን የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችን ብቁነት በተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣሉ።

C. የአከባቢ ትምህርት ቤት ኃላፊነቶች

1. የትምህርት ቤት ሰራተኞች ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የትምህርት ቤት አትሌቲክስን ጨምሮ የሚገኙትን እንቅስቃሴዎች ዝርዝር ለሁሉም ተማሪዎች እና ለወላጆች በጽሑፍ ማሳወቅ አለባቸው።

2. ትምህርት ቤቶች ሠራተኞችን ተማሪዎችን የሚያያሳትፉባቸው ሰፋ ያሉ እንቅስቃሴዎች ሊኖራቸው ይገባል፣ ይህም ተማሪዎች ለሁሉም የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አትሌቲክስ ትምህርታዊ ብቃታቸውን እንዲጠብቁ ወይም እንዲያጠናክሩ ለመርዳት፣ ኮንትራቶችን፣ የማጠናከሪያ ፕሮግራሞችን፣ የማስጠኛ እና የክትትል ፕሮግራሞችን፣ የአካዳሚክ ድጋፍ ትምህርቶችን እና ካውንስሊንግ፣ ከት/ቤት ሠዓት በኋላ የጥናት አዳራሾችን ወይም የተደራሽ ፕሮግራሞች እና/ወይም ሌሎች ፕሮግራሞችን ያጠቃልላል።

3. የትምህርት ቤት ሰራተኞች የድጋፍ መርሃ ግብሮችን ውጤታማነት ለመገምገም ስልቶችን ማዘጋጀት አለባቸው።

**ተዛማጅ ምንጭ፡- የሜሪላንድ** ደንቦች ኮድ §§13A.06.03.01 እና .02

**የደንብ ታሪክ፡-** አዲስ ደንብ ዲሴምበር 18 ቀን 1996 ዓ.ም። ጁን 21 ቀን 2006 ዓ.ም ተሻሽሏል። ፌብሩወሪ 23 ቀን 2007 ዓ.ም ተሻሽሏል፣ኦክቶበር 8 ቀን 2021 ተሻሽሏል።